# ሰማያዊው ጉዞ - የመልአክ ዝማሬ

አጭርና አስደናቂ የገነት ክብር ራእይ

ከፍሬዲ ሄይለር (Freddy Hayler) "*የመላእክት ዝማሬ*" ከተሰኘው ቁጥር 1 ሲዲ ፥ ዝማሬ፡ ሰማያዊ ጉዞ ፥ መዝሙር ቁጥር (ትራክ) 13 ፥ በ [Amazon MP3](Amazon MP3) ላይ ያገኙታል።

አንድ ምሽት በአምልኮ ጥልቀት ውስጥ ሳለሁ ፥ በራእይ በዚህች ምድር ላይ በሕይወቴ ካየሁት በጣም ግዙፍና ፈርጣማ ከሆነው ሰው በአስር እጥፍ የሚተልቅ ግዙፍ መልአክ አየሁ። ወርቃማና የተጠቀለለ ጸጉር ነበረው ፥ ባለ ሰማያዊ ፈሳሽ መብረቅ መሳይ ዓይኖች። ፊቱ እንደጋል አንጸባራቂ ነጭ ምድጃ ነው እንዲሁም በአፉ ውስጥ የተዋበውን ሰማያዊ የገነት ምስጋናን የሚያወጡ የእሳት ልሳኖች አሉት። እናም በድንገት ፥ በግራ እጁ አንጸባራቂ፥ ደማቅ፥ የሚያበራ ወርቃማ ሰይፉን እንደያዘ ቀኝ እጁን በሰሜን ወዳለው ሰማይ ዘረጋ ።

ልብሶቹ በሰማያዊ(ገነታዊ) ቁሶች የተሠራ ነው - በዚህ ምድር ተገኝተውም ሆነ ታይተው በማይታወቁ - ልክ በጣም ምርጥ እንደሆነ ፈትል - ልክ ህያው እንደሆነ ቁስ ዓይነት። መልኩ ፕላቲነም ዓይነት ፥ ብርሃን ከውስጡ እየመነጨ ወደ ውስጥ ይመለሳል ፥ **የፈጣሪ አምላኬን** ልዩ ክብር የሚያወጣ ህያው ብርሃን።

ኦ እናም የተዋሀዱና ተለዋዋጭ የሙዚቃ ቃናዎች በማያቋርጡ ስኬሎችና ከልብሱ ውስጥ እንደ አጃቢዎች ያለ የማይገለጽ ውበት የለው ድምጽ ልክ እንደ ፈሳሽ ምንጭ ይፈልቅ ነበር። ይህ መልአካዊ ፍጥረት **ከሁሉንቻዩ አምላክ** ህልውና ገና እንደመጣ ነበር። በልብሱ ላይ ያሉት የክብር ነጠብጣቦች እስካሁን ድረስ እንደሚያንጸባርቁ አስተዋልሁ እንዲሁም በ**እግዚአብሔር** ክብር ህልውና (Shekinah) ብርሃን እያበሩ። (Shekinah [ሽኪናህ] = የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም የ**እግዚአብሔር** መገኘት ፥ ህልውና ወዘተ. እንደማለት ነው።) እንደዚህ ያለ የከበረ ፍጥረት በእርግጥም እኛ ካለንበት ከዚህ ዓለም እጅግ በሚበልጥ ቦታ በመኖሩ እውነታ ተሸበርሁ። ፊቱ በንግሥና ቅድስና(ንጽሕና) እና አላማ መንፈስ ውስጥ ተነክሯል ፥ እንዲህም ሆኖ በጣም በርኅራኄ አስተያየት ፥ ወደሚንቀጠቀጠው ሰውነቴ ተመልክቶ ጮክ ባለና በግልጽ ድምጽ ፥ "*ና*" አለኝ።

እጄን ያዘኝና ፥ በአንድ አፍታ በታላቅ ፍጥነት ወደ ላይ እየሄድን ነበር ፥ ከአድማስ በስተሰሜን ታላቅ የብርሃን ዙፋን ይታየኛል። በዙፋኑ ዙሪያ ሙሉ ደማቅ ጭጋግና ጉም ነበር ፥ የማይሰላ ርዝማኔ ባለው እንደ ትልቅ ሕንፃ ባለ ደመና ብዙ መብረቆችና ከፍተኛ ነጎድጓድ ታጅቦ። እንዲሁም መላእክት ደስ የሚል ዝማሬን ሲዘምሩና አንዳንዶቹም በሰማይ ላይ እየተገለባበጡ አየሁ።

በድጋሚ በአድማሱ ላይ በርቀት እጅግ ድንቅ የሆነው የከበረው **አምላክና ንጉሥ** በከበረው ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ማየት ይቻላል። እንዲሁም ከዙፋኑ በላይ የተንቆጠቆጠ ቀስተደመና ይገኛል ፥ የእያንዳንዱም ክበብ ርዝማኔ የማይለካ ነው ፥ ለመግለጽ እጅግ በጣም አስደናቂ ነው። በስተሰሜን ምስራቅ ፥ ሰባት ረዣዥም ፥ የቅዱሱ እሳት ምሰሶዎች የተዘረጉባቸው ያጌጡ ተራራዎች በግልጽ ይታዩኛል።

መልአኩም እንዲህ አለኝ፡ "*ይህ ለ**እግዚአብሔር** የራሱ ምርጦች ለወደፊት የተዘጋጀ ቦታ ነው።*" ከዛም መልአኩን ለመንሁት ፥ "*እባክህ ወደ **እግዚአብሔር** ዙፋን ቅርብ ውሰደኝ*" ምክንያቱም ምንም እንኳን በጣም ሩቅ በሆነ ቦታ ቢሆንም **ከህልውናው** የሚወጣው ሕይወትና ፍቅር እንዲሁም ብርሃን ይሰማኝ ነበር። ወደ ቅርብ በተጠጋሁ ቁጥር የበለጠ ህያውነት ፥ የበለጠ ደስታ ይሰማኛል። በህይወቴ ሁሉ እንደዚህ ያለ ሕያውነት ተሰምቶኝ አያውቅም። የሕይወትና ፍቅር እንዲሁም ቅድስናና ፍጹምነት ሁሉ ምንጭ **እግዚአብሔር** ነው። ወደ **እርሱ** መቅረብ በቃላት የማይነገር መደመምን ይፈጥራል።

እናም ወደ **እርሱ** እየቀረብሁ ስመጣ አራቱን እንሰሶች ማየት ስለጀመርሁ በፍርሃት መንቀጥቀጥ ጀመርሁ። እነዚህ ኪሩቤልን የሚመስሉ ፍጥረቶች፥ የ**እግዚአብሔርን** ዙፋን የሚጠብቁ ታላቅና ኃይለኛ ህያዋን ፍጥረታት ፥ የዓለማትን **ጌታ** ያለማቋረጥ የሚያወድሱ። እንዲሁም ብዙውን ዓይኖቻቸውን ማየት እችል ነበር ፥ ወደ ውስጥም ወደ ውጪም፥ ሁሉንም ነገር ማየትና መለየት የሚችሉ። ማንም ቁመታቸውን፥ ስፋታቸውን፥

አስፈሪ ብቃታቸውን ወይም ኃይላቸውን፥ ጉልበታቸውን ወይም የጥንካሬያቸውን ከፍታ መጠን፥ ክብርና ግርማ ሊያውቅም ሆነ ሊገምት አየችልም። ታላቅ የመላእክት ዙፋን በኅብረት የማያቋርጥ ዝም-ብሎ የሚፈስ ዜማን ሲያሰሙ። ወደ ላይ ስመለከት፥ እንደ ተወርዋሪ ኮከቦች ዓይነት በገነት ሰማዮች ላይ ሲወነጨፍ አያለሁ፥ ብዛት ያላቸው ወርቃማ ባለ ብዙ ቀለም ሰረገላዎች ብዛት ያላቸውን በሰማይ ታዋቂ የሆኑትን ይዘው። እንዲሁም እንደባሕር ያሉ መልአካዊ ፍጥረታት ሱራፌልና ኪሩቤል እንዲሁም ሁሉም ዓይነት ሊቃነመላእክትና መላእክት፥ ለመገመት በቁጥር እጅግ የበዙ ሌሎች ብዙዎች፥ ከአራቱ እንሰሳት መካከል በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ክብር ሁሉም እጃቸውን አንስተው ሁሉም የዜማ መሳሪያዎችን እየተጫወቱ።

አእላፋት መላእክት በተዋበና በከበረ ዝማሬ፤ ሚሊየኖች የመላእክት ድምፆች አንድ ላይ ተጣምረው በከፍታና በውህደት አጅበዋቸው እንዲሁም ህሊናን በሚያልፍ አስደናቂ ሰማያዊ ጥራት።

በድንገት ከዙፋኑ በስተቀኝ በኩል **የሰው ልጅን** የሚመስል ተገለጠ፥ በቅጽበት፥ እኔና መልአኩ በጠራው ወለል ላይ በትሕትና እንደሞተ ሰው ተደፋን፥ ታላቅ የሆነ ከፀሐይም የሚበልጥ ሊቀመልአክ በታላቅ ድምጽ "*እነሆ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ አምልኩት!!!!*" እያለ ሲያውጅ፥ የ'ሽኪናህ'ው (የህልውናው፣ ክብሩ) ብርሃን በምድር ሚሊየኖች እና ሚሊየኖች ማይሎች ርቀት ድረስ ይፈስሳል።

እናም በብዙ ውኃዎች ድምፅ፥ እንዲህ አለ፡

***"ጆሮ ያለው ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያኑ የሚናገረውን ይስማ። ከዚህ ዓለም ኑሮ ትምክህት፥ ከሥጋ ምኞት የተለየ እናም ተራውን፥ እግዚአብሔራዊ ያልሆነውን፥ ዓለማዊውን የውሸትና ሰይጣናዊ፥ እርሱም የወደቀው፥ የሆነውን መንገድ የተዉ ብጹአን ናቸው!"***

ከዚያም በድንገት፥ የሚሽከረከረው አውሎ ንፋስ እኛን ወደላይ **እጅግ ቅዱስ ወደሆነው** ዙፋን ከፍ እያረገ ሲያቀርበን የታላቁን ነጎድጓድና ግዙፉ መብረቅ ድምፅ በስሱ ሰማሁት። ማንም ሥጋ በቀጥታ የ**አ**ብን ፊት እንደ **እግዚአብሔርነቱ** ሊመለከት ወይም ሊያይ አይችልም። ምንም እርኩስ በፊቱ መኖር አይችልም። ማንም ሰው በ**እ**ርሱ ፊት አይከብርም(አይደምቅም)። ማንም ሥጋ በህለውናው ፊት አይከብርም። ሆኖም የ**ቅዱሱ አባት** ፊት ጥልቀት ሊብራራ የማይቻልና መለኪያ ወይም ምንም ዓይነት መስፈርት የሌለው ነው። ...

ለእኔ ይህንን ራእይ ማየት ወደ ምንምነት መቅለጥ(መለወጥ) ነበር። ወደ መልአኩ ጮኽኩ፥ እባክህ ህይወቴን አድናት። ... የ**ጌታ** ከንፈሮች እንደ እሣት ምድጃ ናቸውና -- ይህን መግለጫ ምንም ዓይነት ዘይቤም ሆነ ቃል በምድር ላይ አይገኝም። ... የ**አምላካችን** ፊት የማይገለጽ ነው። ... ሆኖም የከበረው ፊቱ ለመላው ዓለም ፍንጣቂና መብረቃዊ ህይወትን ያመነጫል። የ**እግዚአብሔር ፊት** ብርሃን ትሪሊየን ጊዜ ከፀሐይና ከዋክብት ይበራል፥ ቅዱስ ፊቱ እንደ ሰው የሚመስል ነው ነገር ግን ብርሃን አሳላፊና አሸብራቂ (translucent and incandescent) ነው፥ እናም በቃላት ሊገለጽ የማይችል ውብ ነው እንዲሁም ከማንኛውም ንጽጽር በላይ የሚያረካ። እጹብ ድንቅና የማያልቅ ልዩነትና ክብር፥ ከኃያልና ታላቅ ምስጢራዊ የማይገለጽ መጠን ያለው ድምፅ፥ ብዙህን ድምፆችና ቢሊየኖች ትእዛዛት፥ ተመሳሳይ ትእዛዛት፥ ከአፉና ከህልውናው ይመነጫሉ። ቅርጹ ፈጽሞ የማያቋርጥ ዝማሬን በሚያሰሙ በሚሊየኖች መላእክት ሰራዊቶች ይታጀባል። **የሁሉንቻዩ የዘላለሙ አምላክ** ክብር ከአገላለጽ በላይ ድንቅ ነው። (ትሪሊየን - ሚሊየን ጊዜ ሚሊየን ነው፣ ቢሊየን - አንድ ሺህ ጊዜ ሚሊየን ነው)

ከዚያም ይህ አስደናቂ ሊቀመልአክ ወደ እኔ ቁልቁል እያየ "*አዎን ከተመረጡት ቅዱሳን ትንሹ እንኳን የ**ጌታችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ** ወንድም ነው። አዎን፥ እናንተ ራሳችሁ እኛ መላእክት እንኳን ፈጽሞ የማንዘምረውን ዝማሬ ልትዘምሩ ይገባል። በ**ኢየሱስ ክርስቶስ ደም** በኩል፥ ልጆችና የ**እግዚአብሔር** የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ሆናችኋል፥ እናም እናንተ ለዘላለም የተቤዡትን ዝማሬ እየዘመራችሁ ከ**አምላካችን** ጋር ትገዙና ትነግሣላችሁ!*"

እስካሁን ራእዩን ማስታወስና የከበረውን የመላእክቶቹን ዝማሬ ድምጽ እንደገና መስማት እችላለሁ። ... በመላእክቱ ዝማሬ እንደገና ዙፋኑን ማየት ይቻለኛልና። ክብር!! ከዘላለም እስከ ዘላለም **ለእርሱ** ክብር

ይሁን!! ክብር ለኢየሱስ!!!!!! ከመላእክት ጋር ልዘምርልህና ላወድስህ!!! መላእክት ያመልኩህል እኔም አደንቅሀለሁ!!

ክብር ለበጉ!!

## ተጨማሪ ጥቅሶች

*መዝሙር* 103:19-22 እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች። ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ። ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ። ፍጥረቶቹ ሁሉ በግዛቱ ስፍራ ሁሉ፥እግዚአብሔርን ባርኩ። ነፍሴ ሆይ፥እግዚአብሔርን ባርኪ።

*መዝሙር* 104:1-6 ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፤ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ አንተ እጅግ ታላቅ ነህ፤ ክብርንና ግርማን ለበስህ። ብርሃንን እንደ ልብስ ለበስህ፤ ሰማይንም እንደ መጋረጃ ዘረጋህ፤ እልፍኙን በውኃ የሚሠራ፥ ሰረገላውን ደመና የሚያደርግ፥ በነፋስ ክንፍም የሚሄድ፥ መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ፥አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል። ለዘላለም እንዳትናወጥ ምድርን በመሠረትዋ ላይ መሠረታት። በጥልቅ እንደ ልብስ ከደንሃት፥በተራሮችም ላይ ውኆች ይቆማሉ።

*መዝሙር* 148:1-14 ሃሌ ሉያ። እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት፤ በአርያም አመስግኑት። መላእክቱ ሁሉ፥ አመስግኑት፤ ሠራዊቱ ሁሉ፥ አመስግኑት። ፀሐይና ጨረቃ፥ አመስግኑት፤ ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ፥ አመስግኑት። ሰማየ ሰማያት፥ አመስግኑት የሰማያት በላይም ውኃ። እርሱ ብሎአልና፥ ሆኑም፤ እርሱም አዝዞአልና፥ ተፈጠሩም፤ የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑት። ለዘላለም ዓለም አቆማቸው፤ ትእዛዝን ሰጠ፥ አያልፉምም። እባቦች ጥልቆችም ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ከምድር አመስግኑት፤ እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ፥ ቃሉን የሚያደርግ ዐውሎ ነፋስም፤ ተራሮች ኰረብቶችም ሁሉ፥ የሚያፈራም ዛፍ ዝግባም ሁሉ፤ አራዊትም እንስሳትም ሁሉ፥ ተንቀሳቃሾችም የሚበርሩ ወፎችም፤ የምድር ነገሥታት አሕዛብም ሁሉ፥ አለቆች የምድርም ፈራጆች ሁሉ፥ ጕልማሶችና ቈነጃጅቶች፥ሽማግሌዎችና ልጆች፤ የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑ፤ ስሙ ብቻውን ከፍ ከፍ ብሎአልና፥ ምስጋናውም በሰማይና በምድር ላይ ነው። የሕዝቡንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል፤ የቅዱሳኑንም ሁሉ ምስጋና ወደ እርሱ ለቀረበ ለእስራኤል ልጆች ሕዝብ ከፍ ከፍ ያደርጋል። ሃሌ ሉያ።

*መዝሙር* 150:1-6 ሃሌ ሉያ። እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤ በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት። በችሎቱ አመስግኑት፤ በታላቅነቱ ብዛት አመስግኑት። በመለከት ድምፅ አመስግኑት፤ በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት። በከበሮና በዘፈን አመስግኑት፤ በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት። ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት፤ እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት። እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። ሃሌ ሉያ።

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥አሜን።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com